
# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2018 የነበረው
# የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የአፕሪል ወር ለዝናብመፈጠር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛው የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመጠናከራቸዉ ጋር በተያዘ የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በመጣሉ በተለይም በወሩ ሦስተኛዉ አስር ቀናት ላይ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ በማስከተሉ በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን በተደረገው ግምገማ ለመረዳት ተችሏል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ መካከል ለመጥቀስ ያህል በዶሎ ኦዶ 123.9፣ በቡርቃ 102.9፣ በደሎመና 93.2፣ 76.5፣ 45.7 እና 40.0፣ በአሮሬሳ 62.7፣ በጂንካ 74.8፣ 52.5፣ 46.2 እና 36.7፣ በባቲ 74.6፣ በደገሃቡር 70.8፣ 48.5 እና 37.6 ፣ በአማን 68.9፣ በኮንሶ 58.2፣ በቡርጂ 52.1፣ በምዕራብ አባያ 50.4፣ በጂንካ 46.2 እና 36.7፣ በነጌሌ ቦረና 52.4 እና 43.9፣ በተርጫ 42.8፣ በጅግጅጋ 79.4 እና 44.0፣ በወላይታ ሶዶ 58.1፣ 41.0 እና 37.3 በሳውላ 51.5፣ 49.4 እና 43.7፣ በአብአላ 64.8፣ በገዋኔ 50.0፣ በሀገረማርያም 81.2፣ 34.3 እና 30.0፣ በቦሬ 42.1፣ በወራቤ 57.5 በናዝሬት 56.4፣ በሀዋሳ 52.0 እና 34.0፣ በደብረዘይት 55.8፣ አርባምንጭ 36.5፣ በዝዋይ 45.2፣ በአየሁ 38.9፣ በጊኒር 61.1 በሚ.ሜትር ይገኙበታል፡፡


ባለፈው ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፤ በአፋር ክልል ዞን 01፣ 03 እና 04፤ በዋግህምራ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ በጋምቤላ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፣ በምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲና ባሌ እንዲሁም በጉጂና ቦረና ዞኖች ላይ ከ50-390 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ7-20 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች እና ሁሉም የወለጋ ዞኖች ላይ ከ5-25 በሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ3-6 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 6 እና 7)።

ባለፈው የአፕሪል ወር የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና የደቡብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋግህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የአፋር እና ኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ፣ የምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፣ አርሲና ባሌ፣ ጉጂና ቦረና ዞኖች፤ ሁሉም የጋምቤላ እና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 8) ።


ካርታ 6 ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7     ኢ.ኤ.አ   ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ8   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ
መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2018 የነበረው የአየር ጠባይ</u>
# <u>በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባለፈው የአፕሪል ወር ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ነበር፡፡
ይህም በአብዛኛው የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ያዳረሰ ዝናብ ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገታቸው ላይ የጎላ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፤ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም ለደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ፣ ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በተለይም በደቡባዊ አጋማሽ እና በጥቂት የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአንዳንድ ስፍራዎች የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአዝዕርቱ የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን ቢፈጥርም በአንዳንድ ከላይ በተጠቀሱ አካባቢዎች የነበረው ከባድ ዝናብና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (9)፡፡


ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2018 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-30 **ኤፕሪል** 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛው ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የታችኛውና የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛው አፋርደናከል አዋሳኝ ቦታዎች እንዲሁም የላይኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በተጨማሪም አብዛኛው ምስራቃዊው የአባይ አጋማሽ፣ የአዋሽ አዋሳኝ ቦታዎች፣ የባሮአኮቦ የላይኛውና ምስራቃዊው ክፍል፣ ጥቂት የላይኛው አፋርደናከል እንዲሁም የመካከለኛው ዋቢሸበሌና አዋሽ ተፋሰሶች እርጥበታማና ከፊል እርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል$ የተቀሩት የታችኛውና የመካከለኛው አባይ አዋሳኝ ኪስ ቦታዎች፣ የታችኛው ባሮአኮቦ፣ አብዛኛው የተከዜ እና የታችኛው የአፋርደናከል ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 10)።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# **እ.ኤ.አ ከሜይ1-31/2018 የሚኖረው**

# **የአየር ጠባይ አዝማሚያ**

በመደበኛ ሁኔታ  በሜይ ወር ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ከበልግ አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ በመሄድ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች መጠናከር ጋር ተያይዞ ዝናቡ ወደ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይስፋፋል።

በመጪው ሜይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬአቸውን ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢ ላይ እንደሚኖርና በአንዳንድ ሥፍራዎችም ላይ ከባድ ዝናብ የሚዘወተርና አልፎ አልፎ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በሜይ ወር <u>የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል አብዛኛዎቹ ዞኖች፣ ጋምቤላ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ ፣ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ምሥራቅ ሸዋ ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣አርሲና ባሌ፣ቦረናና ጉጂ፤አዲስ አባበ፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣የባህር ዳር ዙሪያ፣ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም እንዲሁም አዊ ዞኖች፤ ከትግራይ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3፣4 እና 5 ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ እንዲሁም አብዛኛው የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ ሀረሪ እና ድሬዳዋ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም ከመደበኛው በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ የሚዘወተር ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል።</u>

## **እ.ኤ.አ ከሜይ 1-31/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ**

## **በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ**

በመጪው ሜይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬአቸውን ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢ ላይ እንደሚኖር ይጠበቃል ይህም ሁኔታ በተለየዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የበልግና የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደሩና ከፊል

አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ለሚገኙ የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ የአዝዕርቱን የውሃ ፍላጎት መሟላትና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ስለሆነ የሚመለከተዉ ክፍል የዉሃ ማቆር ሥራዎችን ቢሠራ በአንዳንድ ማሣዎች ላይ ዕጥረት በሚገጥምበት ጊዜ ዉሃዉን ለመጠቀም ይረዳል። በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን በመስራት ከወዲሁ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ከእርጥበት መብዛት ጋር የፀረ ሰብል ተባይና የአረም መከሰት ሊኖር ሰለሚችል የሚመለከተው ክፍል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ ከወዲሁ ጥንቃቄ እንዲወስድ እንመክራለን፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከሜይ 1-31/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ</u>
## <u>አዝማሚያ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥለው በሜይ ወር ከበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑት ተፋሰሶች በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ዝናቡ እየተስፋፋ እንደሚሄድ ትንበያው ይጠቁማል$ ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ አባይ፣ ተከዜ፣ ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌና ኦጋዴን እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽና አፋርደናከል ተፋሰሶች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል$ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተጠቆመ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአዎንታዊ ጎኑ የወራጅ ውሃ መጠን እንዲጨምር አስተዋፆ ስለሚኖረው ለግድቦችና ለውሃ ማቆሪያ ኩሬዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል$ በሌላ በኩል በነበረው የተራዘመ ደረቅ ሁኔታ መሬቱን ለጎርፍ ተጋላጭ ስለሚያደርገው ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል$ ሆኖም አሁን ያለውን የዝናብ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋልም ሆነ አሉታዊ ጎኑን ለመከላከል ከወዲሁ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡